ኅዳር ፳፮ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም
December 5, 2010

# <u>በቶሮንቶ የሠማዕታት ቀን ተከከበረ</u>

ኅዳር ፳፮ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም ላለፉት ሃያ ዓመት በወያኔ እጅ የተገደሉትን፣ የታሰሩትንና መድረሻቸው የጠፋውን ወገኖቻችን በጋለ መንፈስ ተከብሮ ውሏል። በዕለቱም በወያኔ አጋዚ ነበሰ ገዳዮች የተፈጸመውን አሰቃቂ ግድያ የሚያሳይ በቪድዮ ተቀርጾ ለሕዝቡ ታይቷል።

ከዚህ ባሻገር በደረግ አገዛዝና በወያኔ ገዢ ከመሆኑ በፊት ለዘመናት ለዲሞክራሲ ለሰባዊ መብት ለሕግ የበላይነትና ተገዥነት መቋቋም ብሎም በሕዝብ በተመረጡ መሪዎች አገራችን እንድትሰተዳደር ጥቅማቸውን ወደ ጎን ትተው ያለጊዚያቸው የተሰውትን ሁሉ መተኪያ የማይገኝላቸውን ኢትዮጵያዊያን ዘክረንላቸዎል።

አንድ ወጣት በወቅቱ የወያኔው አጋዚ ጦር በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያደረገውን ፋሽስታዊ ጭፍጭፋ በምስክርነት ለተሰበሰበው ሕዝብ አንዲህ ሲል አሰምቷል።

የግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ወያኔ መሸነፉን አስቀድሞ ስላወቀው የስዓት እላፊ አዋጅ አወጀ። ከአዋጁ አንዱ ሠልፈኛው የቅንጅትን ዓርማ እጣቱን ቢያሳይ በአጋዚ ጥይት ያልምንም ማወላወል እጣቱ እንደሚቀረጥ የወያኔው ቁንጮ መለሰ ዝናዊ በይፋ አወጀ።

ዛቻው ሳይገታው ወጣቱ በአካባቢው ከሚኖሩ ወጣቶች ጋር በመሰባሰብ የተቃውሞው ሠልፍ ለመቀላቀል ወደ ጎጃም ቨረንዳ(መርካቶ) በማምራት "የሕዝብ ድምፅ" አይቀማም የሚለውን መፈክርና የተለያዩ ቀስቀሻና ወቅታዊ መዝሙሮች እየዘመሩ ማስተጋባት እንደጀመሩ በአባዲና ፖሊስ አካባቢ አድፍጦ ሲጠባበቅ የነበራው የአጋዚ ጦር በተኩስ ሠልፉን እንዳስቆመው ሲቃ እየያዘው ገልጾታል። ሠልፈኛው በየአቅጣቸው ሲበታተን ቁጥር 6 እና 20ን አውቶብሶች አቃጠሉት። በአጋዚው ተኩስ ምክንያት ብዙ ሠልፈኞች ቆስለዋል ተገለዋል።

በዚህ ግርግር ከአጋዚው ጥይት ለማምለጥ ሲሞክር አንድ ወጣት እንደ አጋጣሚ የተከፈተ ቤት በር ስላገኘ ዘው ብሎ ገብቶ አመለጣቸው። አንድ የአጋዚ ወታደር ሲሮጥ አይቶት ተከትሎት ከገባበት ቤት ሲደርስ ሁለት ባልና ሚስት አዛውንቶች ያገኛል። ባልን ልጁን እንዲያስረክቡ አፋጦ በመጠየቅ ባል ማንም ሲገባ አላየሁም ምን አድርግ ነው የምትለኝ (በዚህ ጊዜ ተፈላጊው ልጅ አጥሩን ዘሎ ጠፍቷል) እያሉ ቃል ሲለዋወጡ ወታደሩ በያዘው መሣሪያው አዛውንቱን ደረታቸውን በጥይት መታቸው። ሚስት ኡኡ ሲሉ እሳቸውንም ባልተወለደ አንጀቱ በሰደፍ በመምታት ወለሉ ላይ ዘረሮአቸው ጥሎ ወጣ። ባል ወደ ሐኪም መወሰዳቸውን እንጂ ይሙቱ አይሙት ይትረፉ አይተረፉ ግን የማቀው የለም በኋል። ንግግሩን ሲደመድም ግን

ወያኔ የዲሞክራሲ ሥርዓት አስፍኛለሁ ሲል በጋዚጣው፤ በሬድዮና በተሌቪዥኑ ሲመጻደቅ ወያኔ/ኢ.ሕአዴግ በእርግጥም እውነተኛ ገጹን ከሕዝብ አልፎ ለዓለም ያሳየበት ወቅት ነበር አሁን ቢሁን ያው ነው። እኔንም ሌሎችንም ወጣቶች የወያኔ ፋሽሽታዊ ሥራ እንደንመራር ከማድረጉ በላይ ጥቂቶቻችንን በለጋ ዕድሜአችን ወላጆቻችና የምንወዳት አገራችንን ትተን ለስደት ተዳርገናል ሲል አምርሮ ተናግሯል። ወገኖቼ የበሽተኛው፤ የጎጠኛውና የተመጻዳቂው ወያኔያዊ ዴሞክራሲ ይህን ይመስላል።

ከተጋባዥዎቹ የኢ.ሕአፓ (ዴ) ወኪል እንዲህ በለዋል። በኛ እምነት ይህ የሠማዕታት ቀን ብቻ ሳይሆን በክብር የወደቁትን ሠማዕታት ቃል ኪዳን ተሸክሞ የመሄድ በማያወላውል እምነታችን በመጽናት እንዲሁም ተስፋና ብርሃን ፤ የሁላችንም የእምነት ቃል እንዲሆን ያሻል። ይህ ትግል ደግሞ ለሥልጣን ለሚወዳደሩት “በፖለቲካ ድርጅቶች ጫንቃ ላይ የሚጣል ሳይሆን ማንኛውም ኢ.ትዮጵያዊ ትንሹ ትልቁ ለህሊናው ሲል የሚያደርገው ትግል ነው።

ለተጨቆነ፤ ለተራበ፤ ለታረዙ፤ ለታሰሩ፤ለተገደሉ፤ለተሰደዱ መቆምና አለንላቸሁ በማለት የሃይማኖት ተቋሞች፤ የብዝኃን ድርጅቶች፤ የሰባዊ መብት ተሟጓቾች፤ ከሁሉም በላይ እያንዳንዱ ኢ.ትዮጵያዊ ለነፃነቱ ይህን ትልቅ ኃላፊነት ዳር ማድረስ ይኖርበታል። በፖለቲካ በሚል ስብስብ የተሰለፉ የድርጅቶችና የሲቪክ ኃይሎች ኃላፊነት ቀላል ስላልሆነ በህሊናችን ትልቅ ጠባሳ ከማድረሱ በፊት ወደ ፊት የልጅ ልጆቻችን ቢሚጠይቁን ጊዜ የራአሳችን ዜግነት ድርሻ ምን ሠራችሁ ቢሉን እንኳ ማስረዳት ይቸግረናልና ተባብረን እንታገል።

ሰለዚህ ይህን የትብብር የተስፋ፤ የአንድነት እንዲሆን እየተመኘን እኛም ቂም በቀል ሳንል የአመለካከት ልዩነት ሳያግደን ከማንኛውም ኃይል ጋር ለመሥራት ዝግጁ ነን። ይህን ስንል በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባር ለማሳየት ድርጅታችን ከምን ጊዜውም የበለጠ ተግባራዊ እናደርገዋለን በለዋል። ሌሉችም ድርጅቶች እንዲሁ ቃል እንዲገቡ እናበረታታለን ሲሉ ተወካዩ ንገገራቸውነ ቋጭተዋል።

ሌላው ተናጋሪ የኢ.ትዮጵያ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ተወካይ በቶሮንቶ፤ አቶ አከሊሉ ወንድአፈራሁ ነበሩ። እሳቸውም ንግግራቸውን ሲጀምሩ የውያኔ/ኢ.ሕአዴግ አምባ ገነንነት የጀመረው በኢ.ሕአፓ ታጋዮች ላይ በነ ፀጋዬ ገብረ መድኅን፤ ይሳሕቅ ደበር ፀዮን፤ ሥጦታው አምኃና ሌሎች ጭምር ላይ ነበር። አሁንም ቢሆን እኩይ ተግባሩን በሰፊው ቀጥሎበታል። የታቃዋሚ ድርጅት አባሎችን፤ የሰባዊ መብት አስጠባቂ መሪዎችን፤ የሃይማኖት መሪዎችን፤ የሠራተኛወና የመምህራን ማኅበር መሪዎች፤ የተማሪ፤ የአረሶ አደሩ፤የነፃ ጋዚጠኞች መሪዎችና አባሎች በጥቅሉ ለኢ.ትዮጵያ የሞቆረቆሩትንንና ለሕዝብ የሚታገሉትን ያስራል ይገላል።

አገራችን በዓለም የምትታወቀው ያለ ሕግ በማሰር በመግደል በማስቃየት ከሥራ በማባረር የታወቀች ሆናለች። ትግሉ የሁላችንም ነው አገራችን ከወየኔ/ኢ.ሕአዴግ ነፃ የማናወጣበት ምክንያት አይኖረም በጋራ አስከ ታገልናችው ድረስ ብለዋል።

በመጨረሻም እያንዳንዳችን ነፃ ካለሆን ነፃ ለመሆን አንችልም ሲሉ ንግግራችወን ደምድመዋል።

# <u>አትረሱም</u>

ከግንቦት ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ጀምሮ በወያኔ/ኢሕአደግ የታረዳችሁ ፤ የተገደላችሁ ፤

በዱር በገደሉ የተወረወራችሁ ፤ በየስር ቤቱ የታጎራችሁ ፤ ቀይ ባሕር የበላችሁ ፤

በምደረ ዓረብ ያላቃችሁ ፤ በወያኔ እሳት የጋያችሁ ፤ እንዲሁም በደርግ ዘመን የጠፋ

ደብዛችሁ ፤ ቤቱ ይቁጠራችሁ

አትረሳችሁም ኢትዮጵያ አገራችሁ

ቃል ገብተናል በየዓመቱ ልንዘክራችሁ

ቃለ መኻላው ባጭሩ እንዲህ ይላል፦

1ኛ. ልዩነታችን አቻችለን ወያኔን በቁርጠኛነት ለመታገል በወደቁት ሥም ቃል እንገባለን።

2ኛ. ወያኔ ቅንቅን/ምስጥ እንደበላው ግንድ ስለሆነ ጠንካራ ኅብረት በመፍጠር በሕዝብ በተመረጡ ወኪሎች መተካትን ተግባራዊ ለማድረግ አሁንም በተሰውት ሥም ቃል እንገባለን።

3ኛ. በተቃዋሚው ውስጥ ተሰግስገው የገቡትን ሆዳሞችና ባንዳዎች ከመካከለችን በማስወጣትና በማጋለጥ በቁርጠኛነት እናት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ነፃ ለማወጣት አሁንም በተሰውት ሥም ቃል እንገባለን።

በዚህ መልክ የዘንድረውን የሠሰማዕታት ቀን መታሰብያ ስብሰባ ተጠናቋል። ለሚቀጥለው ዓመትም በተሻለና በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ተሰማምተናል።

ድል ለሕዝባችን!!!!